# ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ዜና መጽሄት

# Debre Markos University Newsletter

በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት በየወሩ የሚታተም

Monthly Newsletter Published by the Corporate Communications Directorate

ቅጽ-3 ቁጥር-24 ሚያዚያ ወር 2007 ዓ.ም እትም Volume-3 Number-24 April 2015 G.C Release

ዩኒቨርሲቲው ለአካባቢው ልማት ከሚያደርገው አስተዋጽኦ በተጨማሪ በአገራዊ የልማት ፕሮጀክቶች መሳተፍ ስላለበት ............................2

የማህበረሰብ አገልግሎቱን የበለጠ ለማጠናከርና ማህበረሰቡ በዩኒቨርሲቲው ተጠቃሚነቱን የበለጠ ለማረጋገጥ የማህበረሰብ ሬዲዮ ጣቢያውን ማቋቋም ወሳኝ ነው ........................................6

የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ያደረገው የገንዘብ ድጋፍ 5.7 ሚሊዮን እንደሚጠጋ ..........................................9

ልማዳዊ ድርጊቱና አስተሳሰቡ በተለይም በአለባበሱ፣ በአመጋገቡ እና በቁጠባ ባህሉ ላይ ያለውን ችግር በጥናት ለመፍታት .....................11

## በውስጥ ገፆቻችን

- የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጡ........................................................ 2
- ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የማህበረሰብ አገልግሎት ሬዲዮ ለማህበረሰቡ ከፍተኛ ሚና እንደሚኖረው ተገለፀ............................................................. 5
- ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ዋንጫ ደማቅ አቀባበል አደረገለት................................ 8
- የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በሚያካሂደው ባህል ላይ ያተኮረ ምርምር ዙሪያ የምክክር መድረክ አካሄደ ..................... 11
- የኢትዮጵያ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ስፖርት ማህበር ጥናትና ምርምር ሲምፖዚየም ተካሄደ ....................... 13
- የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ልኡክ ቡድን በህዳሴው ግድብ ጉብኝት አደረገ ................................................ 15
- የሀዲስ አለማየሁ የባህል ጥናት ተቋም የስነ ጽሁፍ ሂስ መድረክ አዘጋጀ................................................. 18



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication

# ራዕይ
# Vision

እ.ኤ.አ. በ2030 ከዓለም ካሉ ታዋቂ ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ ሆኖ መገኘት፡፡

**Debre Markos University aspires to be world class University in 2030.**

# ተልዕኮ
# Mission

ጥራቱን የጠበቀ ትምህርትና ስልጠና በመስጠት ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች ማፍራት

**Producing competent and innovative professionals through providing quality instructional, CoCurricular and cultural involvement.**

አጋር አካላትን በማሳተፍ ችግር ፈች ጥናትና ምርምር ማድረግ፣

Carrying out problem solving research through the active involvement of stakeholders and,

ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የማማከርና የማህበረሰብ አገልግሎት በመስጠት ለሃገራችን ልማት የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ፣

Providing demand driven community and consultancy services.



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication

# የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጡ

በሁሉንአየን ጋሻው



የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ጥላዬ ጌቴ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ባደረገው የገንዘብ ድጋፍ ላይ ለጋዜጠኞች ማብራሪያ ሲሰጡ

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ጥላዬ ጌቴ ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ 4ኛ ዓመት አከባበር፣ የህዳሴው ዋንጫ አቀባበልና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ከጋዜጠኞች ለቀረበላቸው ጥያቄ ሰፊ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥተዋል፡፡

እንደ ዶክተር ጥላዬ ጌታ ገለፃ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ለህዳሴው ግድብ የሚያደርገው ድጋፍ በ2007 ዓ.ም. ዓመታዊ ዕቅድ መሠረት መሆኑን ጠቁመው ዩኒቨርሲቲው ለአካባቢው ልማት ከሚያደርገው አስተዋጽኦ በተጨማሪ በአገራዊ የልማት ፕሮጀክቶች መሳተፍ ስላለበት ዩኒቨርሲቲው በዩኒቨርሲቲው ከሁሉም ኮሌጆችና ዳይሬክቶሬት የተውጣጣ ህዝባዊ ድጋፍ አስተባባሪ ኮሚቴ ተዋቅሮ እየሠራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication

የዩኒቨርሲቲው ህዝባዊ ድጋፍ አስተባሳሪ ኮሚቴ በውስጡ ንዑሳን ኮሚቴዎች አቋቁሞ በርካታ ተግባራትን እያከናወነ ሲሆን በ2007 ዓ.ም. ሊያከናውናቸው ያሰባቸው ተግባራት 4 እንደሆኑ ተገልጿል፡፡

የመጀመሪያው ሙሉ ለሙሉ የተፈፀመው የወሎ ተርሸሪ ኬር ሆስፒታል የተምቦላ ትኬት ሽያጭ፣ ሁለተኛው የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ድጋፍ፣ ሶስተኛው የአማራ አቀፍ ልማት ማህበር እና አራተኛው ለዩኒቨርሲቲው የእግር ኳስ ክለብ ድጋፍ እንዲያደርግ የማስተባበር ዕቅድ ይዞ ኮሚቴው በመንቀሳቀስ ላይ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የዩኒቨርሲቲው መምህራን፣ ሠራተኞችና ተማሪዎች የሚያደርጉትን ድጋፍ ኮሚቴው ሲያስተባብር ቆይቶ የህዳሴው ግድብ ወደ ምስራቅ ጐጃም ዞን መምጣቱን ተከትሎ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲም እንደ አንድ ወረዳ እራሱን ችሎ ለህዳሴው ዋንጫ አቀባበል ለማድረግ የታሰበ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ድጋፍ እንዲያደርግ አመራሩ ትኩረት ሰጥቶ የሰራባቸውን ዶክተር ጥላዬ ሲገልፁ አንደኛ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ የሚያደርገው ድጋፍ ትርጉም ያለው እንዲሆንና ሁለተኛ በህዳሴው ግድብ ዙሪያ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በአባይ ጉዳይ ዘብ መቆም ስላለበት ይህን ለማድረግ ደግሞ ግንዛቤውን ማዳበር ስለሚገባ በተለያዩ ርዕሶች ላይ የፓናል ውይይቶች እንዲደረጉ ዕቅድ ተይዞ ፖናል ውይይቶች በቡሬና በዋናው ግቢ መደረጋቸውን ገልፀዋል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የተሠራው ሥራን ሲገልፁ ዩኒቨርሲቲው እንደ ተቋም የሚገዛውን ቦንድ መወሰን በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው የ1 ሚሊዮን ብር ቦንድ መግዛቱን የገለፁት ፕሬዚዳንቱ የዩኒቨርሲቲው መምህራንና ሰራተኞች በሁለት አመት ተከፍሎ የሚያልቅ ከ2.5 ሚሊዮን ብር በላይ፣ ተማሪዎች ደግሞ በሶስት ሴሚስተር ተከፍሎ የሚያልቅ የ1 ሚሊዮን ብር ድጋፍ ማድረጋቸውን ገልፀዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በህዝባዊ ድጋፍ አስተባባሪ ንዑስ ኮሚቴ እየተሠራ ያለው የዩኒቨርሲቲው መምህራንና ሠራተኞች በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን በአካል እንዲጐበኙ ዕቅድ ወጥቶ ሁለት ዙር በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብንና በአካባቢው የሚገኙ እንደ በለስ የስኳር ልማት ፕሮጀክት ተጓዳኝ የልማት ቦታዎችን እንደሚጐበኙ ገልፀዋል፡፡

ዶ/ር ጥላዬ ጌቴ ዩኒቨርሲቲውን ለየት የሚያደርገው ነገር በህዳሴው ዋንጫ አቀባበሉ ነው ይላሉ፡፡ ዩኒቨርሲቲው ዋንጫውን ከዞኑ 20 ወረዳዎች አንዱ ሆኖ ሲቀበለው ከዋንጫነቱ አልፎ ሌላ ትርጉም ስላለው ያሉት ፕሬዚዳንቱ የቀድሞው የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስቴር ለህዝቡ የሰጡትን አደራ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ምላሽ የሰጠበት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ሌላው ግን የገንዘብ ድጋፍ በሁሉም አካባቢ የሚደረግ ቢሆንም ዩኒቨርሲቲው ግን የታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ 4ኛ ዓመትና የህዳሴ ዋንጫ አቀባበል ሁለገብ በሆነ መልኩ እያከበርን መሆናችን ለየት ያደርገናል ብለዋል፡፡ በዚህም የተማሪዎች፡ የመምህራንና ሰራተኞች የጥያቄና መልስ ውድድር፣ የተሻለ ውጤት ላመጡ ተማሪዎች የማበረታቻ ሽልማት፣ ከታላቁ የህዳሴ ግድብ ጋር የተያያዙና ታሪካዊ ግንኙነት ያላቸውን የህግ ማዕቀፍ፣ ግድቡ ለአረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት ያለውን ፋይዳ፣ ቦንድ በካፒታል ማርኬት ያለውን ጠቀሜታ ወዘተ የሚያሳዩ የውይይት መነሻ ጽሁፎች በዩኒቨርሲቲው መምህራን ተዘጋጅተው መቅረባቸውና ሌሎች በርካታ ዝግጅቶች መኖራቸው ስነ ስርዓቱን ከማድመቃቸው ባሻገር የተለየ እንዳደረጉት ፕሬዚዳንቱ አክለው ተናግረዋል፡፡

ይህ ስራ ዳግም የሁሉም ባለድርሻ አካል መሆኑን ጠቁመው አንድ ዩኒቨርሲቲ ከተሰጡት ተልዕኮዎች የመማር-ማስተማር፣ የምርምርና የማህበረሰብ አገልግሎት ከመስጠት አንፃር የማህበረሰብ አገልግሎት ማለት ይህ ስለሆነ ይህንን አጠናክረን መቀጠል ተገቢ ነው ብለዋል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በአጠቃላይ ላደረገው በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ድጋፍ ምስጋናቸውን አስተላልፈዋል፡፡ ፍቃዳቸውንና ሃሳባቸውን ያልገለፁትን የዩኒቨርሲቲው አካላት ዩኒቨርሲቲው መብታቸውን እንደሚያከብር አክለው ገልፀዋል፡፡

በጋዜጣዊ መግለጫው የዩኒቨርሲቲው የህዝባዊ ድጋፍ አስተባባሪ ኮሚቴ ሰብሳቢ እና የአካዳሚክ ኤክስኪዩቲቭ ደይሬክተር አቶ ታደሰ ጤናው የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ስላደረገው የገንዘብ ድጋፍ መረጃ፣ የምርምርና ህትመት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ደረጀ አደመ ዩኒቨርሲቲው ከገንዘብ ድጋፍ በተጨማሪ ግድቡን ዘላቂ ለማድረግና በደለል እንዳይሞላ ለማድረግ ዳይሬክቶሬቱ በአካባቢ ልማትና በተፈጥሮ ሀብት አያያዝ እየሠራ ያለውን እንዲሁም የአካባቢውን ስነ ምህዳር ለመመለስና ወደ አባይ የሚፈሡ ወንዞችንና ምንጮችን በዘላቂነት ደህንነታቸውን ለመጠበቅ በጮቄ ተራራ ላይ እየተሰራ ስላለው ጥናትና ምርምር ከጋዜጠኞቹ ለቀረበላቸው ጥያቄ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ሌላው የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ በዓል አከባበርን ዩኒቨርሲቲውን ለማስተዋወቅ እና የህዝብ ግንኙነት ስራ ለመስራት የተደረገው እንቅስቃሴ አበረታች እንደነበረ ዳይሬክተሩ ገልፀዋል፡፡

በመጨረሻም የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶክተር ጥላዬ ጌቴ እንደገለፁት የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ከዚህ በፊት አንድ ጊዜ የወር ደመወዙን በአመት በመክፈል ድጋፍ ያደረገ መሆኑን አስታውሰው አሁን ለሁለተኛ ጊዜ ያደረገው ድጋፍም አበረታች ነው ብለዋል፡፡ ስለሆነም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ የሚያደርገው የቦንድ ግዥ ድጋፍ ግድቡን እኛው በእኛው እንገነባዋለን ስላልን አንድም ቁጠባን ባህል እያደረግን ነው በሌላ በኩል ደግሞ ሁሉን የኢትዮጵያ ህዝብ ያሳተፈ ግድብ እየገነባን በመሆኑ ይህ ተጠናክሮ መቀጠል ይገባዋል ብለዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ የሚጠበቀው ስለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ወቅታዊና ተጨባጭ መረጃ በመያዝ በቅድሚያ እራሳችን ተገንዝበን ሌሎች እንዲያውቁትና እንዲገነዘቡት የማድረግ ስራ ይጠበቃል ብለዋል፡፡ እንዲሁም በተለያየ ጊዜና ሁኔታ በተለያዩ የሀገራችንና ውጭ ሀገሮች ስንቀሳቀስ እያንዳንዳችን ለአገራችን ዲፕሎማቶች ሆነን ልንሰራ ይገባል በማለት መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

## ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የማህበረሰብ አገልግሎት ሬዲዮ ለማህበረሰቡ ከፍተኛ ሚና እንደሚኖረው ተገለፀ

በሁሉንአየን ጋሻው





0913-14-96-80 Fax: 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication

### የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የማህበረሰብ ሬዲዮ ጣቢያን ለማቋቋም በብቸና ከተማ ወረዳ የማህበረሰብ ድጋፍ ሲሰበሰብ

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ እያከናወናቸው ካሉት ተልዕኮዎች መካከል አንዱ የሆነውን የማህበረሰብ አገልግሎት ለሁሉም የአካባቢው ማህበረሰብ ተደራሽ በሆነ መልኩ በብቃት ለመስጠትና ለመተግበር የማህበረሰብ ሬዲዮ ጣቢያ ለማቋቋም የሚያስችለውን የማህበረሰቡን ድጋፍ በተለያዩ የአካባቢው ወረዳዎች በመንቀሳቀስ መረጃውን ባሰባሰቡበት ወቅት የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የሬዲዮ ጣቢያው የሚኖረውን ከፍተኛ ሚና ገለፁ፡፡ ዩኒቨርሲቲው በመማር ማስተማሩ፣ በምርምርና በማህበረሰብ አገልግሎት እንዲሁም በቢዝነስ ስራዎች እያከናወናቸው ያሉ ተግባራትን ለአካባቢው ማህበረሰብ በዜና መጽሔት፣ በበራሪ ወረቀቶች፣ በአመታዊ አብርሆት መጽሔትና በዩኒቨርሲቲው ድረ ገጽ ሲያስተላልፍ መቆየቱን ያስታወሱት የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ምስጋናው ጋሻው የማህበረሰብ አገልግሎቱን የበለጠ ለማጠናከርና ማህበረሰቡ በዩኒቨርሲቲው ተጠቃሚነቱን የበለጠ ለማረጋገጥ የማህበረሰብ ሬዲዮ ጣቢያውን ማቋቋም ወሳኝ ነው ብለዋል፡፡ የሬዲዮ ጣቢያው ዩኒቨርሲቲው እያከናወናቸው ያሉ ተግባራትና የምርምር ውጤቶች እንዲሁም የቴክኖሎጂ ሽግግር ለመፍጠር ያስችላል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የማህበረሰቡንና ዩኒቨርሲቲውን ትስስር ለማጠናከርና በጋራ ለዕድገትና ልማት ለመስራት እንደሚያስችል እምነታቸውን ገልፀዋል፡፡ ለዚህም ዩኒቨርሲቲው የማህበረሰብ ሬዲዮ ጣቢያውን ለማቋቋም የሚያስችለውን የማህበረሰብ ድጋፍ ፊርማ የማሰባሰብ ሥራ በብቃት ተሠርቷል ብለዋል፡፡

የብቸና ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አቶ ደምመላሽ አቤና እንደገለፁት ዩኒቨርሲቲው የሬዲዮ ጣቢያውን ማቋቋሙ ዩኒቨርሲቲዎች ከተሰጧቸው ተልዕኮዎች መካከል የአካባቢውን ማህበረሰብ ከማገልገል አንፃር አርሶ አደሩን በግብርናው፣ ነጋዴውን በንግዱ እንዲሁም ሌሎችን ተጠቃሚ ከማድረግ አንፃር ቴክኖሎጅዎችን የማስተዋወቅ ስራ ለመሥራት የሚያስችል ሲሆን ከአካባቢው ማህበረሰብ የሚነሡ የተለያዩ ጥያቄዎችንም ከዩኒቨርሲቲው ሙሑራን ምላሽ ለማግኘት የሚያስችል ነው ብለዋል፡፡ በአጠቃላይ የአካባቢው ማህበረሰብም ዩኒቨርሲቲውም በጋራ የሚጠቀሙበት



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication

እንደሚሆን እምነታቸውን ገልፀዋል፡፡ ስለሆነም ዩኒቨርሲቲው የአካባቢውን ማህበረሰብ ችግሮች ለይቶ ጥናትና ምርምሮችን በመስራት ችግሮችን መቅረፍ የሚያስችል ፕሮግራም ቢዘረጋ ህብረተሰቡም ያለውን ችግር በግልጽ በማሳየት ከዩኒቨርሲቲው የሚሰጠውን ትምህርት በአግባቡ ተቀብሎ ወደ ተግባር መለወጥ ይኖርበታል ብለዋል፡፡

የደጀን ወረዳ የመንግስት ኮሙኒኬሽን ተወካይ ኃላፊ አቶ ሰለሞን አሻግሬ እንደገለፁት ዩኒቨርሲቲው የሬዲዮ ጣቢያውን ማቋቋሙ በአካባቢው የሬዲዮ ጣቢያዎች ያልተስፋፉበት ሁኔታ ስላለ የህብረተሰቡን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ አንድምታ ለማሳደግ ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡ የሬዲዮ ጣቢያው እንዲቋቋም ዩኒቨርሲቲው ለጣቢያው የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን የማሟላት ስራ እና የአካባቢው ማህበረሰብ ደግሞ ፕሮግራሞችን የመከታተልና ወደ ተግባር የመለወጥ ኃላፊነት አለበት ብለዋል፡፡ ይህን የማህበረሰብ ሬዲዮ እንዲቋቋም ሁሉም ህብረተሰብ በባለቤትነት ይዞ ድጋፍ እንዲያደርግ እና ዩኒቨርሲቲውም ከግብ እንዲያደርሰው መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡ በማህበረሰብ የድጋፍ ፊርማ አሰባሰብ ሂደትም ከ1000 በላይ የሚሆኑ የአካባቢው ማህበረሰብ በብቸና፣ በደጀን፣ በየጁቤና በቡሬ ድጋፋቸውን በፊርማ እንደገለፁ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በመጨረሻም ለማህበረሰብ ሬዲዮ ጣቢያው ማቋቋሚያ ድጋፍ የሰጡ የአካባቢው ማህበረሰብ እንደገለፁት ዩኒቨርሲቲው የሬዲዮ ጣቢያውን ማቋቋሙ እየሰራቸው ያሉ የተለያዩ ተግባራትን ለህብረተሰቡ ለማድረስ እንዲሁም ህብረተሰቡ የሚያነሳቸውን ጉዳዮች ለዩኒቨርሲቲው ለማድረስ ያስችለዋል ብለዋል፡፡ ይህም ማህበረሰቡ ተገቢውን መረጃ ለማግኘት እንደሚያስችለው አክለው ገልፀዋል፡፡

በተያያዘ ዜና "የማህበረሰብ ሬዲዮ ጣቢያው ይቋቋማል፣ የማህበረሰቡ የመረጃ ፍላጎትም ይሟላል" በሚል መሪ ቃል በኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀው 2 ገጽ በራሪ ወረቀት በብቸና፣ ደጀንና የጁቤ ነዋሪዎች ተሰራጭቷል፡፡ በራሪ ወረቀቱም ስለ ዩኒቨርሲቲው ዳራ፣ ራዕይና ተልዕኮ፣ የትምህርት ፕሮግራሞችና ስታፍ፣ የጥናትና ምርምር ስራዎች፣ የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎች፣ የቢዝነስ ሥራዎችና የማህበረሰብ ሬዲዮ ምንነት መረጃ እንደሚሰጥ ለማወቅ ተችሏል፡፡

# ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ዋንጫ ደማቅ አቀባበል አደረገለት

በሁሉንአየን ጋሻው




ዩኒቨርሲቲው የታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ዋንጫ በተቀበለበት ወቅት የደ/ማ/ዩ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ጥላዬ ጌቴ የመክፈቻ ንግግር ሲያደርጉ

ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ዋንጫ ከምስራቅ ጐጃም ዞን 20 ወረዳዎች ተጨማሪ 1 ወረዳ በመሆን ዋንጫውን ከፍተኛ የፌደራል፣ የክልል፣ የዞንና የወረዳ የመንግስት የስራ ኃላፊዎች፣ ዕውቅ ሙሑራን፣ የከተማዋ ነዋሪዎች፣ የዩኒቨርሲቲው መምህራን፣ ሰራተኞችና ተማሪዎች እንዲሁም የከተማዋ የተለያዩ ትምህርት ቤት ተማሪዎችና ሌሎች አካላት ከአማራ የፖሊስ ማርሽ ቡድን ባንድ ጋር በመተባበር መጋቢት 25 ቀን 2007 ዓ.ም. በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ደማቅ አቀባበል አደረጉለት፡፡ በዕለቱም የአማራ ክልል ፖሊስ ማርሽ ቡድን ለክቡር አቶ ብናልፍ አንዷለም የክብር ሰላምታ አቅርቧል፡፡



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication

በዋንጫ አቀባበል ስንስርዓቱ ላይ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ጥላዬ ጌቴ እንደገለፁት የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ያደረገው ድጋፍ ከፍተኛ በመሆኑ ይህ ሊበረታታ ይገባል ብለዋል፡፡ ሀገራችን የበለፀጉ ሀገሮች የደረሱበትን መንገድ ለይታለች ለዚህም የህዳሴ መንገድ ተቀይሶ የሀገሪቱ ፖሊሲ ግብርና መር ኢንዱስትሪ ሆኖ ትላልቅ ፕሮጀክቶች በሚገባ በማጤን ህዝቡ በፕሮጀክቶች ላይ የጋራ እርብርቡን አጠናክሮ መቀጠሉን ገልፀዋል፡፡ ከትላልቅ ፕሮጀክቶች መካከል አንዱና ዋናው የህዳሴው ግድብ በማን፣ እንዴትና በምን

አይነት ሁኔታ እንደሚገነባ ህብረተሰቡ የሚያውቀው የአደባባይ ሚስጥር መሆኑን በማስታወስ ህዝቡ እስካሁን ባደረገው ብሔራዊ አንድነትና እንቅስቃሴም የአይቻልምን ስሜት የገለሰሰ፣ የአንድነትን ስሜት የፈጠረ ተምሳሌታዊ ሀውልት የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን እየገነባ ነው ብለዋል፡፡ ስለሆነም የታሪካችንን መቀየሪያ ይህን ቅርስ ለማጠናቀቅ ድጋፋችንን አጠናክረን መቀጠል ይገባል ብለዋል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የዩኒቨርሲቲው መምህራንና ሰራተኞች የአንድ ወር ደመወዛቸውን በሁለት አመት ከፍለው ለማጠናቀቅ ቃል መግባታቸውንና ተማሪዎችም ከምግባቸው በመቀነስ ከለገሡት ጋር ዩኒቨርሲቲው ያደረገው ድጋፍ ከ5.7 ሚሊዮን ብር በላይ መድረሡን ጠቁመዋል፡፡ ስለሆነም ድጋፋችንን አጠናክረን በመቀጠልና በጋራ ለአንድ ዓላማ ጉዟችንን በማስቀጠል በህዳሴያችን ድህነት የታሪክ ብቻ ማስተማሪያ ይሆናል ብለዋል፡፡ የአንድነታችን ተምሳሌት የሆነውን የህዳሴ ግድብ “እንዳጋመስነው፣ እንጨርሰዋለን፣ ሌላ እንጀምራለን” ብለዋል፡፡

በተያያዘ ዜና በ2007 ዓ.ም. የአንደኛው መንፈቅ ዓመት የተሻለ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች የማበረታቻ ሽልማት ተሰጥቷቸዋል፡፡ የሽልማት ስነስርዓቱ ከታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ መሠረተ ድንጋይ የተጣለበትን 4ኛ ዓመትና የህዳሴው ዋንጫ አቀባበል ስነስርዓት እየተካሄደ ባለበት ወቅት መሆኑ ተማሪዎችን የበለጠ ውጤታማ እንዲሆኑ ለሥራ የሚያነሳሳና ለህዳሴው ግድብ የሚያደርጉትን ድጋፍ አጠናክረው ለመቀጠል የሚያስችል መሆኑን ተሸላሚዎች ገልፀዋል፡፡ ኢትዮጵያ የጀመረችውን የህዳሴ ጉዞ አስቀጥለው ለመሄድም ተማሪዎች ከፍተኛ ድርሻ እንደሚጠበቅባቸው ተጠቁሟል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ለታላቁ ህዳሴ ግድብ ያደረገው ድጋፍ በዩኒቨርሲቲው የህዝባዊ ድጋፍ አስተባባሪ ኮሚቴ ሰብሳቢ እና የአካዳሚክ ኤክስኪዩቲቭ ዳይሬክተር አቶ ታደሰ



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication

ጤናው በየትምህርት ክፍሉ፣ በየኮሌጁ፣ በየዳይሬክቶሬቱና አጠቃላይ በዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ የተደረገው የገንዘብ ድጋፍ ግልጽ ሪፖርት ቀርቧል፡፡ በሪፖርቱም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ያደረገው የገንዘብ ድጋፍ 5.7 ሚሊዮን ብር እንደሚጠጋ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በፕሮግራሙ ላይ በኮሌጆች መካከል የገመድ ጉተታ ውድድር፣ "ኢትዮጵያዊ" በሚል ርዕስ ተማሪ መልካሙ መነባንብ፣ ግጥምና ሌሎች ዝግጅቶች የቀረቡ ሲሆን ሁሉም ለዝግጅቱ ድምቀት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማበርከታቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በመጨረሻም የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳድር፣ የትምህርት ቢሮ ኃላፊና የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ስራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ ክቡር አቶ ብናልፍ አንዱአለም ባደረጉት የመዝጊያ ንግግር የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ያደረገው የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ 4ኛ ዓመትና የህዳሴው ዋንጫ አቀባበል ስነስርዓት ለኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ፋናወጊ በመሆኑ ልዩ ትርጉም አለው ብለዋል፡፡ በአለፉት 4 ዓመታት ህዝቡ ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የሚያደርገውን ድጋፍ አጠናክሮ መቀጠሉንና የህዳሴው ዋንጫ በአማራ ክልል የ1 ዓመት ቆይታው በተለያዩ ዞኖችና ወረዳዎች የሚያደርገውን እንቅስቃሴ አጠናክሮ መቀጠሉን ገልፀዋል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የህዳሴው ዋንጫ በመሥራቅ ጐጃም ዞን በሚያደርገው ቆይታ ሂደት ዩኒቨርሲቲው ለዋንጫው ያደረገለት ትልቅና ደማቅ አቀባበል እንዲሁም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ያደረገውን የገንዘብ ድጋፍ አድንቀዋል፡፡ እንደ እርሳቸው ገለፃ የህዳሴው ግድብ በተለይ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተለየ ጠቀሜታ አለው፡፡ ስለሆነም ግድቡ ለተማሪዎችና ለመምህራን የምርምር ማዕከል ሆኖ ስለሚያገለግል ሚናው የጐላ ነው ብለዋል፡፡ ዩኒቨርሲቲው ዛሬ ለህዳሴው ዋንጫ አቀባበል እያደረገ ያለው ትልቅ የዲፕሎማሲ ስኬት የተደረሰበት በመሆኑ ከሌሎች ጊዜያቶች ሁሉ ይህ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲን የተለየ ያደርገዋል ብለዋል፡፡

የህዳሴው ግድብ የአንድነታችን ተምሳሌት ከመሆኑ ባሻገር ሀገራችን ቁልቁል ወደ ድህነት ከማሽቆልቆል ወጥታ ወደ ብልጽግና የምታደርገው ጉዞና ወደ አደጉ አገሮች ተርታ ለመሰለፍ የህዳሴ ጉዞ መስመር ይዛ እንቅስቃሴ እያደረገች ባለችበት ዘመን ህዳሴያችን እውን እንዲሆን ለህዳሴው ግድብ የጀመርነውን ድጋፍ በወኔ እጃችን ለአንድም ጊዜም ሳይታጠፍ በመቀጠል ይህንን አጠናቀን ሌሎችን ለመጀመር መትጋት ይኖርብናል ብለዋል፡፡ ስለሆነም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ እያደረገ

ያለውን ድጋፍ አጠናክሮ እንዲቀጥል መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡ "እንደጀመርነው አጋምሰነዋል፣ እንጨርሰዋለን" ብለዋል፡፡

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ 4ኛ አመትና የህዳሴው ዋንጫ አቀባበል በቡሬ ካምፓስና በዋናው ግቢ ከመጋቢት 23-25 ቀን 2007 ዓ.ም. በተለያዩ ዝግጅቶች የተከበረ ሲሆን በዝግጅቶችም የተለያዩ የፌደራል፣ የክልል፣ የዞንና የወረዳ የመንግስት ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች፣ ምዕሁራን፣ የከተማዋ ነዋሪዎች፣ የተለያዩ የከተማው ትምህርት ቤት ተማሪዎች፣ የዩኒቨርሲቲው መምህራን፣ ሰራተኞችንና ተማሪዎች እንዲሁም የአማራ ክልል ፖሊስ ማርሽ ቡድን

በበዓሉ አከባበር ላይ እንደተገኙ ለማወቅ ተችሏል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብም ታላቁን የኢትዮ ህዳሴ ግድብ የደረሰበትን ደረጃ በአካል ለማየት ጉብኝት እንደሚያደርግ ለማወቅ ተችሏል፡፡

## የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በሚያካሂደው ባህል ላይ ያተኮረ ምርምር ዙሪያ የምክክር መድረክ አካሄደ

በሰለሞን አበበ



ዶ/ር ንጉሴ ምትኩ የደ/ማ/ዩ አካ/ጉ/ም/ ፕሬዚዳንት የምክክር መድረኩን ከባለድርሻ አካላት ጋር ሲያካሂዱ

**ደ/ማ/ዩ፡-** የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የጐጃም ህዝብ አለባበስ፣ አመጋገብ እና የቁጠባ ባህል ላይ በሚያካሂደው ምርምር ዙሪያ የምክክር መድረክ ከአማራ ክልል ባህል ቱሪዝም ቢሮ፣ ከፌዴራል

የመንግስት ፋይናንስ ኤጀንሲ፣ ከምስራቅ ጐጃም ዞን አስተዳደር፣ ከምስራቅ ጐጃም ዞን ባህል ቱሪዝም መምሪያ፣ ከምስራቅ ጐጃም ዞን ጤና ጥበቃ መምሪያ እና ከጐጃም ልማት ማህበር ተጋብዘው ከመጡ ባለድርሻ አካላት ጋር የምክክር መድረክ አካሄደ፡፡

የምክክር መድረኩን በንግግር የከፈቱት የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት ዶ/ር ስማቸው ጋሻዬ እንዳሉት የአርሶ አደሩን አኗኗር ስንመለከት ከውስጣችን ይቆጨናል፡፡ ህብረተሰቡ አስተሳሰብ ላይ ምንድን ነው ያለው ችግር? የሚለው ሁላችንንም የሚያስጨንቀን ጉዳይ ነው፡፡ ልማዳዊ ድርጊቱና አስተሳሰቡ በተለይም በአለባበሱ፣ በአመጋገቡ እና በቁጠባ ባህሉ ላይ ያለውን ችግር በጥናት ለመፍታት ከሶስዬሎጂ፣ ከሳይኮሎጂ፣ ከፎክክሎር እና

ከኢኮኖሚክስ ትምህርት ዘርፎች በተውጣጡ ሙህራን ጥናቱን ለማጥናት ተጀምሯል፡፡ ዩኒቨርሲቲው ጥናቱን ቢያጠናም የህብረተሰቡን ችግር ብቻውን ሊፈታ አይችልም፡፡ ከዚህ አንፃር ከኢፌዲሪ የመንግስት ፋይናንስ ኤጀንሲ፣ ከጐጃም ልማት ማህበር እና የአካባቢው ጉዳይ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ ጥናቱን መልክ አስይዞ መስራት ይጠበቅብናል፡፡ ስለሆነም ወደ ተግባር ለመግባት ከባለድርሻ አካላት ጋር የምክክር መድረክ ተዘጋጅቷል ብለዋል፡፡

እንደ ዶ/ር ስማቸው ገለፃ የምክክር መድረኩ ዋና አላማ የችግሩን ግዝፈት እና ጥልቀት በመረዳት የጋራ ግንዛቤ ለመያዝ፣ ለጥናቱ ተገቢ ግብዓት ለመስጠት እንዲሁም የባለድርሻ አካላት ድርሻችንን ይዘን ችግሩን ለመፍታት እንድንንቀሳቀስ ማገዝ ነው በማለት ጨምረው ገልፀዋል፡፡

በምክክር መድረኩ ላይ የምስራቅ ጐጃም፣ ምዕራብ ጐጃም እና አዊ ብሄረሰብ ህዝቦችን አለባበስ ፣ አመጋገብ እና የቁጠባ ባህል ዙሪያ የሚያጠነጥነውን የጥናቱ ፕሮፖዛል ዶ/ር ወሀቤ ብርሀን አቅርበዋል፡፡ በቀረበውም የጥናት ፕሮፖዛል መነሻነት ባለድርሻ አካላት የተለያዩ አስተያየቶች ሰጥተዋል፡፡ ከተሰጡት አስተያየቶች ውስጥም የምስራቅ ጐጃም ዞን ዋና አስተዳደር አቶ ምግባሩ ከበደ እንዳሉት ጥናቱ የዞኑን ህዝብ የአለባበስ፣ የአመጋገብ እና የቁጠባ ባህል በጥልቀት እንደሚገልጽ ያላቸውን እምነት ገልፀዋል፡፡ እንደ አቶ ምግባሩ የጥናቱ ርዕስ የዞናችንን ውስብስብ ችግር የሚዳስስ ስለሆነ በዚህ ዘርፍ ጥናት ለመስራት ዩኒቨርሲቲው መነሳቱ የሚበረታታ ነው፡፡ አቶ ምግባሩ ጨምረው



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication

እንደገለፁት በጥናቱ "የሰው መግደል ባህል" እና "ከሀዘን ጋር ተያይዞ አለቃቀስ ልማዳችን" በጥናቱ ቢካተቱ የሚል ማጠናከሪያ ሃሳብ ሰጠዋል፡፡

በመጨረሻም ዶ/ር ንጉሴ ምትኩ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚዳንት እንዳሉት በምክክር መድረኩ የተነሱትን ሀሳቦች በማካተት የጥናቱ ፕሮፖዛል ተከልሶ ወደ ስራ ይገባል የተሰጠው ሀሳብ ባጠቃላይ ጥናቱን ሙሉ አድርጎ አጥኝዎችን የተሟላ ምልከታ እንዲኖራቸው ያግዛል ብለዋል፡፡ በተለይም አሉ ዶ/ር ንጉሴ የሴቶች የስራ ጫና በዚህ ዘመን ያልተሻገርነው ችግር ነው ስለሆነም በጥናቱ እንዲካተት ይደረጋል ብለዋል፡፡ በተጨማሪም በእለታዊ ግጭት አርሶ አደሩ ላይ የመገዳደል ሁኔታ አለ እዚህ ላይም ትኩረት ይሰጠዋል ብለዋል፡፡ እንደ ዶ/ር ንጉሴ ገለፃ የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ላይ በጥንቃቄ በደንብ ታቅዶ ቢሰራ ጥሩ ነው በማለት ጨምረው ገልፀዋል፡፡

## የኢትዮጵያ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ስፖርት ማህበር ጥናትና ምርምር ሲምፖዚየም ተካሄደ

**ሙሀመድ ሰኢድ**

የኢትዮጵያ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ስፖርት ማህበር ጥናትና ምርምር ሲምፖዚየም በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ተካሄደ፡፡




ክቡር አቶ ያየህ አዲስ ሲምፖዚየሙን በንግግር ሲከፍቱ



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication

በጥናትና ምርምር ሲምፖዚየሙ መክፈቻ ላይ የእለቱ የክብር እንግዳ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ስፖርት ኮሚሽን ኮሚሽነር ክቡር አቶ ያየህ አዲስ በሀገራችን ያለው የስፖርት እንቅስቃሴ እድገት የህዝቡን ፍላጎት አለመመጣጠን ለመቅረፍና የስፖርቱን ልማት ለመደገፍ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የስፖርቱን እድገት ለማፋጠን ጠንክረው ሊሰሩ ይገባል ብለዋል፡፡ እንደ እርሳቸው ገለጻ ስፖርት የህዝብ ማንነት መገለጫ ብሎም ኢኮኖሚያዊ መጠቀሚያ ነው፡፡

በመሆኑም ህዝቡ ያለውን ፍላጎት ለማርካት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ዩኒቨርሲቲዎች በጀት መድበው ሥራዎችን እየሰሩ መሆናቸውንና ለውጥ መታየት መጀመሩን ጠቁመዋል፡፡ በቀጣይም ሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች በስፖርቱ ረገድ እየመጣ ያለውን ለውጥ በስፖርታዊ ጨዋነትም እንዲጎለብት ለማድረግ ሊሰሩ ይገባል ብለዋል፡፡ የኢትዮጵያ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ስፖርት ማህበር ሊቀመንበር አቶ አባይ በላይነህ በበኩላቸው የሀገራችንን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ጥናትና ምርምሮች ከፍተኛ ዋጋ እንዳላቸው ገልጸው፣ ስፖርት ሳይንስ ነክ ጥናቶች በቀጣይ ተጠናክረው ሊቀጥሉና የተጠኑ ጥናቶችም ከመደርደሪያ ማሞቂነት ወርደው ወደተግባር እንዲለወጡ መሰራት እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

ለዚህም በአሁኑ ሰዓት የስፖርት ማህበሩ በተደራጀ ሁኔታ መዋቀሩ ሥራዎችን አቀናጅቶ በውጤት ለመስራት ያግዛል ብለዋል፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ጥላዬ ጌቴ በበኩላቸው በእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግራቸው ላይ ዩኒቨርሲቲው በመማር ማስተማር ከሚያከናውናቸው ተግባራት በተጨማሪ በስፖርታዊ ውድድሮች ረገድ በአራት ዘርፎች እንደሚሰራ ጠቁመዋል፡፡ ከነዚህም መካከል ዩኒቨርሲቲው ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ እግር ኳስ ክለብን በማቋቋም በብሔራዊ ሊግ የሰሜን ምዕራብ ምድብ በሶስተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ፣ በማህበረሰብ አገልግሎት ሥርም በአካባቢው የሚገኙ 35 ታዳጊ ወጣቶችን በማሰባሰብ ትጥቅና አሰልጣኝ በማሟላት የታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክት ማቋቋሙ፣ እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ዘንድም የውስጥ ለውስጥ ውድድር ማካሄድና እንደ ሌሎች ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በስፖርት ፌስቲቫሎች ላይ መሳተፍ እንደሚገኙበት አስረድተዋል፡፡

በስፖርት ማህበሩ የጥናትና ምርምር ሲምፖዚየም መክፈቻ ላይ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ታዳጊ ወጣቶች እግር ኳስ ፕሮጀክት እውቅና የተሰጠ ሲሆን ሰልጣኞችም በእለቱ የክብር እንግዳ የአማራ ክልል ስፖርት ኮሚሽን ኮሚሽነር ክቡር አቶ ያየህ አዲስ፣ የኢትዮጵያ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ስፖርት ማህበር ሊቀመንበር አቶ አባይ በላይነህ እና በዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ጥላዬ ጌቴ መልዕክት ተላልፎላቸዋል፡፡



### ዶ/ር ጥላዬ ጌቴ ለታዳጊ ወጣቶች መልዕክት ሲያስተላልፉ

በእውቅና አሰጣጥ ስነስርዓቱ ላይ ዶ/ር ጥላዬ ታዳጊ ሰልጣኞች ከስልጠናው ባሻገር በአጠቃላይ ስነምግባራቸውና በአካዳሚክ ውጤታቸው ሞዴል ሆነው እንዲሰሩ ያሳሰቡ ሲሆን የአማራ ክልል ስፖርት ኮሚሽን ኮሚሽነር ክቡር አቶ ያየህ በበኩላቸው ዩኒቨርሲቲው በታዳጊ ወጣቶች ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራቱ እጅግ እንደሚያስመሰግነው ገልጸው ሌሎች ዩኒቨርሲቲዎችም ይህን ተሞክሮ በመውሰድ እንዲያበለጽጉ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል፡፡ ታዳጊ ወጣቶችን ለውጤት ለማብቃትም የክልሉ ስፖርት ኮሚሽን ዩኒቨርሲቲው የሚጠይቀውን የገንዘብ የእውቀትና የቁሳቁስ ድጋፍ እንደሚያደርግ ቃል ገብተዋል፡፡ ስፖርት ማህበሩ ፕሬዚዳንትም የዩኒቨርሲቲው ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችን ውጤታማነት ለማሳደግ የሚሰሩ ጥናትና ምርምሮችን እንደሚደግፉ ገልጸው ታዳጊ ወጣቶችን በ9ኛው የኢትዮጵያ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ስፖርት ፌስቲቫል ተሳታፊ እንደሚያደርጉ ቃል ገብተዋል፡፡ በሲምፖዚየሙ ላይ 16 ጥናታዊ ጽሁፎች ቀርበው ውይይት ተካሂዶባቸዋል፡፡

በመጨረሻም የጥናትና ምርምር ሲምፖዚየሙ ተሳታፊዎች ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ምርምር የሚያካሂድበትን የጮቄ ተፋሰስ ልማትና የዩኒቨርሲቲውን ዋና ግቢ የጎበኙ ሲሆን በቆይታቸው መደሰታቸውን ገልጸዋል፡፡ በተያያዘ ዜና በሲምፖዚየሙ ላይ በሊቢያ ውስጥ በአይኤስአይኤስ ለተገደሉ ኢትዮጵያውያን የህሊና ጸሎት ተደርጓል፡፡



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication

# የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ልኡክ ቡድን በህዳሴው ግድብ ጉብኝት አደረገ

በሁሉንአየን ጋሻው

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ልኡካን ቡድኖች በሁለት ዙር ከ17-18/08/2007 ዓ.ም. እና ከ24-25/08/2007 ዓ.ም. በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ጉብኝት አደረጉ፡፡



ለደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ልኡካን ቡድኖች፣ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ስራ አስኪያጅ ኢንጅነር ስመኘው በቀለ የእንኳን ደህና መጣችሁና ስለ ግድቡ መረጃ በሰጡበት ወቅት

የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳቤ ግድብ በራ አበኪያድ ኢንድነር በመነው ዘቀለ ለደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የልኡካን ቡድኖች ባደረጉት የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር የኢትዮጵያ ህዝብ ከሊቅ እስከ ደቂቅ ሁሉንም አንድ አድርጎ በጋራ እንድንዘምር ያደረገ ትልቅ ፕሮጀክት ነው ብለዋል፡፡ በዚህም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ያደረገውን ድጋፍና ግድቡ ያለበትን ሁኔታ በአካል ማየት መቻላቸው የበለጠ መነሳሳትን እንደሚፈጥርላቸው እምነታቸውን ገልፀዋል፡፡ ሁሉም ዜጋ የነገይቱን የኢትዮጵያ ህዳሴ የሚያረጋግጥልንን ግድብ ለመጨረስ በጀመረው አግባብ አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል ያሉት ኢንጅነሩ ግድቡ የኢትዮጵያን የአትችልም መንፈስን የሰበረ፣ ዓለም ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለከት ያደረገ በመሆኑ ከፍተኛ ሚና አበርክቶልናል ብለዋል፡፡ በህዳሴው ግድብ 400 የውጭ መሀንዲሶች እየሰሩ ያሉ ሲሆን የአገራችን መሀንዲሶች የዕውቀት ሽግግር የፈጠሩበትና ክህሎት ያዳበሩበት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ኃላፊ፣ ዶ/ር ሙላቱ ታከለ በህዳሴው ግድብ ጉብኝት ላይ እንደተናገሩት የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ከሚያደርገው ድጋፍ በተጨማሪ ግድቡ ያለበትን ሁኔታ በማየት በቦታው ተገኝቶ ጉብኝት ለማድረግ የሄደ መሆኑን

ገልፀው ዩኒቨርሲቲው በተለያየ መልኩ ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የተለያዩ መረጃዎችን ለማህበረሰቡ ለማድረስና ትስስር ለመፍጠር ታስቦ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

በዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ኤክስኪውቲቭ ዳይሬክተር እና በዩኒቨርሲቲው የህዝባዊ ድጋፍ አስተባባሪ አብይ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ታደሰ ጤናው እንደገለፁት የጉብኝቱ ዓላማ በዋናነት የህዳሴው ግድብ 4ኛ ዓመት አከባበርና የዋንጫ አቀባበል ስነስርዓት አንዱ አካል በመሆኑ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ያደረጉትን የገንዘብ ድጋፍ ለምን እንደዋለና የግድቡን ሁኔታ በአካል ተገኝተው እንዲጎበኙት ለማድረግ ነው፡፡ የጉብኝቱ ተሳታፊዎች አመራሮች፣ መምህራን፣ ሰራተኞችና ተማሪዎች መሆናቸው ደግሞ ሁሉም ለግድቡ እውን መሆንና የሀገሪቱን ህዳሴ ለማረጋገጥ የሚጠበቅባቸውን ሚና ለመወጣት እንዲችሉ ግድቡን በአካል ማየታቸው የበለጠ እንደሚያነሳሳቸው ገልፀዋል፡፡ በዚህ ዓመት ለመጎብኘት ተራ ያልደረሳቸው የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብም በቀጣይ ዕቅድ ተይዞ ጉብኝት እንደሚያደርጉ አቶ ታደሰ አክለው ገልፀዋል፡፡ ዋናው ነገር እንደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ስለህዳሴው ግድብ ተገቢውን መረጃ ለህብረተሰቡ ማድረስና ግንዛቤውን በማጉላት የጀመረውን ድጋፍ አጠናክሮ እንዲቀጥል የማድረግ ኃላፊነት አለብን ብለለዋል፡፡



የ1ኛው ዙር ጉብኝት ተሳታፊዎች በከፊል

በዩኒቨርሲቲው የመጀመሪያው ዙር የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ጉብኝት ልኡክ ቡድን ተሳታፊ የነበሩት ወ/ሮ ያምሮት ድልነሳ፣ ወ/ሮ ሀረግነሽ ብዙነህ፣ ወ/ሮ አይናለም አሥራት እና ወ/ሮ


0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication

መስታወት መስፍን እንደገለፁት በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ መደመማቸውንና ያደረጉት የእስካሁኑ የገንዘብ ድጋፍ ከፕሮጀክቱና ለሀገሪቱ ከሚኖረው ብሩህ የህዳሴ ጉዞ አንፃር ሲለካ እዚህ ግባ የማይባል መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ስለሆነም ግድቡ እስኪያልቅ ድረስ ድጋፋቸውን አጠናክረው እንደሚቀጥሉ እምነታቸውን ገልፀዋል፡፡ ሌሎች ዕድሉ ላልገጠማቸው የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብም ስለግድቡ ሁኔታ በቂ መረጃ እንደሚሰጧቸውና ለቀጣይ እንዲጎበኙት እንደሚያነሳሷቸው ገልፀዋል፡፡ በአቀረቡት የማጠቃለያ ሃሳብም "እንዳጋመስነው እንጨርሰዋለን፣ ህዳሴያችን ዕውን ይሆናል" ብለዋል፡፡

በተያያዘ ዜና የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ልኡካን ቡድኖች በሁለቱም ዙሮች የጣና በለስ ስኳር ልማት ፕሮጀክትንና ዘንገና ሀይቅን እንደጎበኙ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በጉብኝታቸውም የጣና በለስ ስኳር ልማት ፕሮጀክትን የሥራ እንቅስቃሴ፣ ዓላማዎች፣ ለአካባቢው ማህበረሰብ ያለውን ፋይዳ፣ በፕሮጀክቱ የተገነቡ ህዳሴ፣ ፓዊና አሉኩሪንድ ት/ቤቶች መሆናቸውን ለማየት መቻላቸውን ጎብኝዎች ጠቁመዋል፡፡ ፕሮጀክቱ 17190 ለሚሆኑ የአካባቢው ማህበረሰብ የሥራ ዕድል በመፍጠር ከ10.96 ሚሊዮን ብር በላይ በመቆጠብ ኑሮአቸውን በአግባቡ እንዲመሩ ማስቻሉን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ፕሮጀክቱ ሙሉ በሙሉ ስራውን ሲጀምር ለ69,000 ዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር እንደሚያስችል ተገልጿል፡፡

በመጨረሻም በሁለቱ የጉብኝት ዙሮች ተሳታፊ የነበሩት የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ በአጠቃላይ 400 ያህል እንደነበሩ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በቀጣይ አመትም ተራው ያልደረሳቸው የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ጉብኝት እንደሚያደርጉ ተጠቁሟል፡፡

## የሀዲስ አለማየሁ የባህል ጥናት ተቋም የስነ ጽሁፍ ሂስ መድረክ አዘጋጀ

በሰለሞን አበበ





*መምህር ተሰራ አስማረ ከደ/ማ/መ/ኮ፣ አቶ ፈንታ ሁሴን ከደ/ማርቆስ መሰናዶ ከፍተኛ 2ኛ ደ/ት/ቤት እንዲሁም መምህርት አፀደ ማሩ ከደ/ማ/መ/ትም/ኮ የሂስ መድረኩን ሲመሩ*

**ደ/ማ/ዩ፡-** የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ሀዲስ አለማየሁ የባህል ጥናት ተቋም እያሳተመ ያሰራጫቸውን ሀዲስ ዓዲስ ቅጽ 1.ቁ.1፣ ሀዲስ ዓዲስ ቅጽ 1.ቁ2 እና ሀዲስ ዓዲስ ቅጽ 1.ቁ.3 የስነ ጽሁፍ መድብሎች ላይ ያተኮረ የሂስ መድረክ የዩኒቨርሲቲው መምህራን እና ተማሪዎች፣ የደብረ ማርቆስ መምህራን ኮሌጅ መምህራን፣ የደብረ ማርቆስ መሰናዶ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መምህራን እንዲሁም ከተለያዩ የትምህርት ተቋማት የተጋበዙ እንግዶች በተገኙበት አካሄደ፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አካዳሚክ ጉዳዮች ኤክስኪዩቲቭ ዳይሬክተር አቶ ታደሰ ጤናው የሂስ መድረኩን በንግግር ሲከፍቱ እንዳሉት የሀዲስ ዓለማየሁ የባህል ጥናት ተቋም ከተቋቋመ ጀምሮ በርካታ ተግባራት እያከናወነ ይገኛል፡፡

የባህል ተቋሙ የታላቁን ደራሲ የሀዲስ ዓለማየሁን የስነጽሁፍ ስራዎች አጉልቶ በማውጣት ወጣቱ ትውልድ እንዲማርባቸው ከማድረጉም በተጨማሪ የስነጽሁፍ እና የድራማ መድረኮችን በማዘጋጀት አማተር ፀሀፍትና ከያንያን ችሎታቸውንና ክህሎታቸውን እንዲያጐለብቱ ምቹ መደላደል የመፍጠር ስራዎችን ሲሰራ መቆየቱን አውስተዋል፡፡ እንደ አቶ ደርጄው አየነው የሀዲስ አለማየሁ የባህልና ጥናት ተቋም የስነጽሁፍ ባለሙያ ገለፃ የስነ ጽሁፍ ሂስ መድረኩ ዓላማ የታተሙ መድብሎች ለስነጽሁፍ እድገትና ለሌሎች አማተር ደራሲያን የሚጫወቱትን ሚና ማሳየት፣ የግጥም መድብሎች ለአካባቢው ማህበረሰብ የንባብ ፍላጐት እርካታ እና ማህበራዊ ጉዳዮችን ከመዳሰስ አኳያ ምን ያህል አስተዋጽኦ እንዳላቸው ማስገንዘብ፣ የግጥም መድብሎች ተቋሙ ለተነሳበት አላማ ግብ መቺነታቸውን ማረጋገጥ፣ የአማርኛ ቋንቋና ስነጽሁፍ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚማሩትን የንድፈ ሃሳብ ትምህርት በተግባር



**0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64** ✉ **269** E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication

እንዲያረጋግጡ ማድረግና ለሌሎች አማተር ደራሲያን የስነጽሁፉን ሂስ መድረክ በግብአትነት እንዲጠቀሙ ማድረግ ነው ብለዋል፡፡

ከደብረ ማርቆስ መምህራን ኮሌጅ የመጡትና ሀዲስ ዓዲስ ቅጽ 1.ቁ.1ን የሂሱት መምህርት አፀደ ማሩ እንዳሉት የሃዲስ ዓዲስ ቅጽ1፡ቁ1 መድብል የማህበረሰቡን ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ታሪካዊ ጉዳዮችን የሚዳስስ ነው፡፡ ነገር ግን ከዘመናችን አስተሳሰብ አንፃር የስርዓት ፆታን እኩልነት የሚያውጁ እና የሚያስተምሩ የስነጽሁፍ ስራዎች በባህል ተቋሙ የስነጽሁፍ ባለሙያዎች ተመርጠው ቢጨመሩ እንዲሁም ሴት ደራሲያንን በማበረታታት የማካተት ስራዎች ቢሰሩ የተሻለ ነው ብለዋል፡፡

በሃዲስ ዓዲስ ቅጽ1፡ቁ፡2 ላይ ስነጽሁፋዊ ሂስ ያቀረቡት የደብር ማርቆስ መሰናዶ ከፍተኛ 2ኛ ደ/ት/ቤት የአማርኛ ቋንቋ መምህር አቶ ፈንታ ሁሴን እንዳሉት በመድብሉ ያሉት ግጥሞች ማህበራዊ ጉዳዮችን ከመዳሰስ አንፃር የነበራቸው ፋይዳ የጐላ ነው፡፡ የንባብ ባህል እንዲዳብር ከማድረግ አንፃር የስርጭቱ ተደራሽነት አነስተኛ መሆንና ጽሁፎች ደቃቃ መሆን ግን የጐደለው ነገር እንዳለ ያሳያል በማለት ገልፀዋል፡፡ በሌላ በኩል በመድብሉ ውስጥ ያሉት የግጥም ስራዎች በጥቂት ደራሲያን መያዛቸው የአማተር ደራሲያንን የእድል በር ይዘጋል በማለት አቶ ፈንታ ገልፀዋል፡፡

በሐዲስ ዓዲስ ቅ.1፡ ቁ፡3 ስነጽሁፋዊ ሂስ ያቀረቡት ከደብረ ማርቆስ መምህራን ኮሌጅ የመጡት የቋንቋ መምህር አቶ ተሰራ አስማር እንዳሉት በቅ1፡ቁ.3 የታተሙት ስራዎች በጠቅላላ ግጥም መሆናቸውን

ገልፀው እነዚህ ጽሁፎች ሲዘጋጁ የተቋሙ አላማ ማስተማር፣ ማሳወቅና ማትጋት ነበር ብለዋል፡፡ በተጨማሪም በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን ህፀፃች የሚያሳዩ ነበሩ በማለት ገልፀዋል፡፡

በመጨረሻም ከተሳታፊዎች የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበው ስነ ጽሁፋዊ ሂስ ያቀረቡ መምህራን ምላሽና ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡ በስነ-ጽሁፍ ሂስ ፕሮግራሙ ሲሳተፉ ያገኘናቸው የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የማህበራዊና ስነ ሰብ ኮሌጅ ዲን ዶ/ር በለጠ ያዕቆብ በሰጡን አስተያየት በዩኒቨርሲቲው የመጀመሪያ የሆነው ይህ የስነ ጽሁፍ ሂስ ፕሮግራም አንባቢን የሚያበረታታ እና ፀሃፊያንን የሚያተጋ ነው ብለዋል፡፡ መጽሀፍ መታተማቸው ብቻ በቂ አይደለም ለውጥ መኖር አለበት ለውጥ እንዲኖር ደግሞ በባለሙያዎች እነዚህ የስነጽሁፍ ስራዎች ሃሳብ እየተሰጠባቸውና ጠንካራና ደካማ ጐናቸው እየተለዩ



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication

የተሻለ የሚሆኑበት እና የተሻለ ዜጋ የምንፈጥርበትን ሁኔታ የሚያመቻቹ ስለሆነ የሚበረታታ ነው በማለት ዶ/ር በለጠ ያዕቆብ ጨምረው ገልፀዋል፡፡



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication